በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

እ.ኤ.አ 2026 የክረምት ወቅት አጋማሽ የአየር

ጠባይ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

እ.ኤ.አ. ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2026 የነበረዉ የአየር ጠባይ ግምገማ

እንዲሁም ከኦገስት 1 እስከ ሴፕቴምብረ 30/2026 የሚኖረው የአየር

ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦገስት 2026

አዲስ አበባ

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

1. እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2026 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና በቀሪዎቹ የክረምት ወራት የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

አጠቃላይ

ለዘንድሮ የክረምት ወቅት የአየር ጠባይ ትንበያ ከመስጠቱ አስቀድሞ በትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ መካከለኛውና ምሥራቃዊ ክፍል ላይ ቀደም ባሉት ወራት የነበረውና በመጪዉ የክረምት ወቅት የሚኖረው የባህር ወለል ሙቀት ሂደት ላይ ሳይንሳዊ ትንታኔና ጥናት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ ምሥራቃዊ ክፍል የባህር ወለል የሙቀት መጠን ለውጥን፤ የአሃዛዊና ዳይናሚካል የሞዴል ትንበያዎችን መሰረት በማድረግ በይበልጥ ከመጪው ክረምት ጋር ከፍተኛ መመሳሰል እንደሚኖረው እና ይህንን መሠረት በማድረግ ሁለት ተመሳሳይ ዓመታት ተመርጠዋል፤ እነዚህም እ.ኤ.አ 1997፣ እና 2023 ናቸው።

በክረምት ወራት የፓስፊክ ውቅያኖስ የባህር ወለል የሙቀት መጠን ከመደበኛዉ በላይ የመሞቅ (ENSO EL NINO) እንዲሁም የሰሜናዊ ህንድ ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት ከመደበኛው በላይ የመሞቅ (Positive IOD) ተጽዕኖ ስር ሆኖ ሊቆይ እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በህንድና አትላንቲክ ውቅያኖሶች ከፍተኛ የአየር ግፊቶች (High pressure cells) እንዲሁም ሌሎች የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በክረምት ወቅት የሚጠበቀው የዝናብ መጠንና ሥርጭትን አስመልክቶ ትንበያው ተሰጥቷል።

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ባለፉት ሁለት የክረምት ወራት የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና በቀሪዎቹ ሁለት ወራት ሊኖር የሚችለው የአየር ጠባይ አዝማሚያ እንዲሁም በግብርናው በዉሃ ሴክተሮች እና በጤና ላይ አሳድሮ የነበረው የዳሰሳ እንዲሁም ወደፊትም ሊፈጥር በሚችለው አዎንታዊ እና አሉታዊ ተፅእኖ ላይ ጽሁፍ ቀርቧል።

1.1 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2026 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

በዘንድሮው የክረምት ወቅት የዝናቡ አጀማማር በደቡብ ምዕራብና ምዕራብ ቀደም ብሎ የጀመረ ሲሆንና፤ በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚዎች ላይ ደግሞ መደበኛ ፊሩን ተከትሎ ጀምሯል፡፡ በመሆኑም ባለፉት ሁለት ወራት የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ የዉሃ

አካል ከመደበኛዉ በላይ የመሞቅ (ENSO-EL NINO) የተስተዋለበት ሲሆን፣ የህንድ ውቅያኖስ ሰሜናዊዉ ክፍሉ የውሃ አካል በ (Positive IOD) ክስተት ስር መሆኑ ከደቡብ ንፍቀ ክበብ የምድር ወገብን አቋርጦ ወደ ሀገራችን የሚገባው እርጥበት አዘል አየር አዎንታዊ አስተዋጽኦ ነበረው፡፡ወ

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ባለፉት የጁንና የጁላይ የክረምት ወራት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ እና በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ከመደበኛ በላይ ዝናብ የተስተዋለ ሲሆን፤ በመካከለኛው፣ በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በታች ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በሌላ በኩል በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ቦታዎችም ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ በ24 ሰዓት ተመዝግቧል፡፡ በአጠቃላይ ባለፈዉ በጁን እና ጁላይ ወር በ138 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ፡ ፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ50.0-122.4 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡

ባለፉት ሁለት የክረምት ወራት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ የመካከለኛዉ፣ የምዕራብና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ አዲስ አበባ ላይ ከ200-820 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ20-56 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ በተጨማሪም በሸገር ከተማ፣ አርሲ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሀረርጌ ዞኖች፤ የሰሜን ሸዋ ዞን፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜን እና የደቡብ ወሎ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ ምስራቅ፣ ደቡብ ምስራቅና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ወላይታ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ ዞኖች፣

ላይ ከ101-300 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ7-20 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)።

ባለፉት ሁለት የክረምት ወራት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ክልል የምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ አዊ፣ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከትግራይ ክልል የምዕራብና ሰሜን ምዕራብ ትግራይ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ፣ ጠምባሮ ፣ አዲስ አበባ ላይ በአብዛኛዉ ከመደበኛ ጋር የተቀራረበና በጥቂት ቦታዎች ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡ በሌላ በኩል በምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ ዞኖች፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፤የደቡብ የመካከለኛዉ፣ የምስራቅና የደቡብ ምስራው ትግራይ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ጋሞ፣ ወላይታና ባስኬቶ ዞኖች፣ መደበኛና ከመደበኛ በታች ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡



ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2026
ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

1.2 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2026 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ሁለት ወራት በደቡብ ምዕራብ፤ በምዕራብ፤ በሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛው የሀገሪቱ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ የተመዘገበው የእርጥበት ሁኔታ በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ አዎንታዊ አስተዋፅኦ ነበረዉ። ይህም ሁኔታ ለተለያዩ የመኸር ሰብሎች ዘር ለመዝራትና የማሳ ዝግጅት ለማከናወን እንዲሁም ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች የውሃ ፍላጎትን መሟላት የጎላ ጠቀሜታ ነበረው። በተለይም የነበረው እርጥበት በመጠንም ሆነ በስርጭት እየተሻሻለ የመጣበትና ሁሉንም ያዳረሰ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ከጁን ጀምሮ የዘር ጊዜና የማሳ ዝግጅት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች በወቅቱ ለመዝራት አመቺ ሁኔታ የፈጠረ ሲሆን፤ ዘግይተዉ ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከሚሟላት አንፃር የጎላ ጠቀሜታ ነበረው። በተጨማሪም ከኤፕሪል ጀምሮ ቀደም ብለው ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች በተገቢዉ ሁኔታ

እድገታቸዉን እንዲቀጥሉ የጎላ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ በተጨማሪ በአርብቶ አደርና በከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች ላይ በወቅቱ አጋማሽ የተገኘው እርጥበት ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅዖ ከማበርከቱም በላይ ሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ምንጮችን ከማጎልበት አንፃር በጎ ጎን ነበረው፡፡

በአንጻሩ ደግሞ በጥቂት የሰሜን ምስራቅና የምስራቅ አካባቢዎች ላይ የነበረው አነስተኛ በመጠን ያለው እርጥበት በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በአንዳንድ የምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የእርጥበት መብዛት የነበረ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት፣ የአፈር መሸርሸር የማስከተል አቅም እንደነበረው የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በአጠቃላይ ባሳለፍናቸው ሁለት የክርምት ወራት (ጁን እና ጁላይ) የተገኘው እርጥበት ለመኸር አብቃይና ተጠቃሚ አከባቢዎች የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ ላይ በአብዛኛው አዎንታዊ አስተዋፅኦ የነበረው ሲሆን በሌላ በኩል ግን በጥቂት የሰሜን ምስራቅና የምስራቅ አካባቢዎች ላይ የእረጥበት ማነስና የዝናብ መቆራረጥ ጋር ተያይዞ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ጎን ነበረው (ካርታ 4)።



ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁን እስከ ጁላይ 2026
የነበረው የእርጥበት

1.3 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2026 የነበረው የአየር ጠባይ በዉሀዉ ዘርፍ የነበረው ተጽዕኖ

እ.ኤ.አ ከጁን እስከ ጁላይ 2026 በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ በጣም ከፍተኛ የገፀ ምድር ውሃ ስርጭት እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በተለይም በአባይ፣ በባሮ አኮቦ፣ በመካከለኛውና በታችኛው ተከዜ፣ በላይኛው ኦሞ ጊቤ እና በጥቂት በላይኛው የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር ውሃ ሽፋን ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የወንዞችን ፍሰት እንዲጨምር፣ የግድቦችን የውሃ ክምችት እንዲያሻሽል እንዲሁም በተፋሰሶች ውስጥ የሚገኙ አነስተኛ የውሃ ማከማቻዎች በቂ የውሃ መጠን እንዲይዙ ከማድረጉም በተጨማሪ የከርሰ ምድር የውሃ መጠንም ሆነ የመስኖና የሃይል ማመንጫ ግድቦች ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ የውሃ መጠን እንዲኖራቸው ከማስቻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው (ካርታ 5)።



ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁን እስከ ጁላይ በተፋሰሶች ላይ የነበረዉ የእርጥበት ሁኔታ

1.4 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2026 የነበረው የአየር ጠባይ በጤናው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ሁለት የክረምት ወራቶች በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብ፣ የሰሜን፣ የሰሜን ምሥራቅ እና የማዕከላዊ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይ የተስተዋለው የዝናብ፣ የሙቀት እና የእርጥበት ጥምረት ለወባ ትንኝ መራባትና ለበሽታው ስርጭት ምቹ እንደነበር የተተነተኑ የጤና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች የሳያሉ፡፡ በአጠቃላይ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ እና በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፣ በአብዛኛው የጋምቤላ ክልል፣ በሁሉም የምዕራብ ኦሮሚያ ዞኖች፣ በአንዳንድ የሸዋ ዞኖች፣ በሁሉም የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ በሁሉም የምዕራብ አማራ ዞኖች እና በአብዛኛው የትግራይ ክልል ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ የሚደርስ ለወባ መፈጠርና መስፋፋት ምቹ የሆነ የአየር ሁኔታ ነበራቸው (ካርታ 6 ሀ)። በሌላ በኩል ባሳለፍናቸው የክረምት 2026 የመጀመሪያ ሁለት ወራት የነበረውን የአየር ሁኔታ በሰው ልጅ ጤና፣ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ እና በእንስሳት ምርትና ምርታማነት ላይ ከሚያሳድረው ተጽዕኖ አንፃር ሲገመገም፣ የነበረው የአየር ጠባይ በእንስሳት ምርታማነት ላይም ሆነ በጤናቸው ላይ ጉልህ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳልነበረው የተተነተኑ መረጃዎች ያመለክታሉ(ካርታ ለ)። በአንፃሩ በሰው ጤና እና በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ላይ በአንዳንድ ዝቅተኛ ከፍታ ያላቸው አካባቢዎች የሙቀት ጭንቀት ተስተውሏል። በተለይም በአብዛኛው የአፋር፣ የጋምቤላ እና የሶማሌ ክልሎች እንዲሁም በመተሐራ፣ በአርባ ምንጭ፣ በመተማ እና በቋራ ወረዳዎች ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ የሚደርስ አስጨናቂ የሙቀት ሁኔታ መኖሩ በትንተናው ተረጋግጧል (ካርታ 6ሐ)።



ካርታ 6ሀ ባሳለፍነው የክረምት አጋማሽ ወራት የነበረው የአየር ጠባይ ለወባ ትንኝ መራባት ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ



ካርታ 6ለ ባሳለፍነው የክረምት አጋማሽ የነበረው የአየር ሁኔታ በሰዎች ጤና ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ



ካርታ 6ሐ ባሳለፍነው የክረምት አጋማሽ የነበረው የአየር ሁኔታ በእንስሳት ጤና ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

2. እ.ኤ.አ ከኦገስት 1/2026 እስከ ሴፕቴምብር 31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ዝናብ በኦገስት ወር በተጠናከረ ሁኔታ ቀጣይነት የሚኖረዉ ሲሆን የወቅቱ የመጨረሻዉ ወር በሆነዉ በሴፕቴምበር ግን ዝናብ ሰጪ የአየር ሁኔታ ክስተቶች መዳከም የሚጀምሩበት ነዉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከሴፕተምበር የመጀመሪያዉ ሳምንት ጀምሮ ዝናቡ ከሰሜን ምሥራቅና ከምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀስ በቀስ መልቀቅ የሚጀምርበትና ወደ ደቡባዊ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚስፋፋበት ወር ነዉ፡፡ በአጠቃላይ በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት ወር ዝናቡ ተጠናክሮ የሚቀጥልበት ወር ሲሆን በሴፕተምበር ወር በፀሐይ ሀይል ታግዘዉ ከሚፈጠሩ ጠንካራ የደመና ክምችቶች በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ አልፎ አልፎ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የመከሰት ዕድሉ ከፍተኛ ነዉ፤

ባለፉት ሁለት የክረምት ወራቶች በትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ ምስራቃዊውና የመካከለኛው ክፍል የባህር ወለል የሙቀት መጠን ከመደበኛ በላይ የመሞቅ ሁኔታ (ENSO - El Niño) ስር የቆየ ሲሆን በቀሪዎቹ የክረምት ወራትም ቀጣይ እንደሚሆንና በበጋ ወቅትም ከመደበኛው በላይ የመሆን እድሉ እስከ97% እንደሚሆን መረጃዎች ያመላክታሉ።

በተጨማሪም የሰሜናዊ ህንድ ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት አሁን ላይ በ (positive IOD) ስር እንደሚገኝ ሲሆን በቀሪዎቹም ወራት (positive-IOD) ሆኖ ይቀጥላል፡፡ በአጠቃላይ በሚቀጥሉት ሁለት ወራት (ኦገስት እና ሴፕቴምበር) በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭት በተለይም በኦገስት ወር እንደሚጠናከሩ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በፀሀይ ሀይል ታግዘው ከሚፈጠሩ ጠንካራ ደመናዎች ከባድ ዝናብ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ሊዘወተር ይችላል፡፡ የክረምቱ አወጣጥም በደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብና መካከለኛወ የሀገሪቱ አከባቢዎች መደበኛዉን ፊር ተከትሎ እንደሚወጣ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚዎች ላይ ደግሞ ከመደበኛ ፊሩ በተወሰነ ቀናት ቀድሞ እንደሚወጣ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በመሆኑም በቀጣዮቹ ሁለት የክረምት ወራት (ከኦገሰት እስከ ሴፕቴምበር 2026)፣ ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት እየተጠናከሩ ሊሄዱ እንደሚችሉ አዝማዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከሚጠናከሩት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛዉ የሃገሪቱ ቦታዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር አዝማዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በፀሐይ ሀይል ታግዘዉ ከሚፈጠሩ የደመና ክምችቶች በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በረዶ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በሌላ በኩል በሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ ክቀላል እስከ መካከለኛ የዝናብ መጠን ያገኛሉ ካርታ (7 እና 8)፡፡



ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 - ሴፕቴምብር 2026 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 1 ሴፕቴምብር 2026 የሚኖረው የዝናብ መጠን ከረጅም ግዜ አማካይ

2.1 ከኦገስት 1/2025 እስከ ሴፕቴምብር 30/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኦገስት እና ሴፕቴምበር ወራቶች በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛዉ የሃገሪቱ ቦታዎች ላይ የሚጠበቀው ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት በመኸር አብቃይና ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ለግብርና ስራ እንቅስቃሴ አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው ይጠበቃል። ይህም ሁኔታ በመኸር ወቅት ለሚመረቱ ለመካከለኛና ረጅም ጊዜ ሰብሎች እድገት፣ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት፣ ዘግይተዉ ለተዘሩ የመኸር ሰብሎች እንዲሁም ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። በሌላ በኩል አልፎ አልፎ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ የሚጠበቅ በመሆኑ በዚህም ምክንያት ውሃ የሰብል ማሳዎች ላይ እንዳይተኛ የውሃ ማፍሰሻ ቦዮችን አስቀድሞ ማዘጋጀትና ማፅዳት፣ የማንጣፋፍና የመከላከል ስራ መስራት እንዲሁም አረምን በወቅቱ ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-

ተባይ ኬሚካሎችን በወቅቱ ከግብርና ባለሙያ በሚያገኙት ምክረ ሀሳብ በመደገፍ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የአፈር መሸርሸርና የመሬት መንሸራተት ሊከሰት ስለሚችል ለዚህ ስጋት ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎችን በመለየት እና ግንዛቤ በማስጨበጥ የአደጋ ተጋላጭነትን እና ሊደርስ የሚችል የተያያዥ ስጋትን ለመቀነስ የሚያስች የተቀናጀ የቅድመ ጥንቃቄ ስራ ከወዲሁ ማከናወን ይመከራል፡፡ በሌላ በኩል በሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው የእርጥበት የሚጠበቅ በመሆኑ የሚገኘውን ዕርጥበት በጥንቃቄ መጠቀምና በፀሐይ ሙቀት ምክንያት የሚፈጠረውን የውሃ ትነን (Evaporation) መቀነስ እንዲሁም ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት እጥረት እንዳይከሰት ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በመከከለኛዉ፣ በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚዎች ላይ ደግሞ የዝናብ ሁኔታዉ ከመደበኛ ፈሩ በተወሰነ ቀናት ቀድሞ እንደሚወጣ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፣ ስለሆነም የሚገኘዉን ዝናብ በሰው ሰራሽም ሆነ በተፈጥሮ የውሃ ማጠራቀሚያዎች በማከማቸት በደረቅ ሰሞናት ጥቅምላይ እንዲያውሉ ይመከራል። በአጠቃላይ በግብርናው ሴክተር ላይ ያሉ የሚመለከታቸው አካላት በቀሪ ሁለት የክረምት ወራት ያሉትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀምና ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስ የሚያስችል በቂ ዝግጅት በማድረግ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚስችል ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል።

2.2 ከኦገስት 1/2025 እስከ ሴፕቴምብር 30/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀጣዮቹ ሁለት የክረምት ወራት በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ እጅግ በጣም ከፍተኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት እንደሚኖር ይጠበቃል። በተለይም በአብዛኛው መረብጋሽ፣ ተከዜ፣ አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ የላይኛው እና መካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ እንዲሁም የላይኛው ዋቢ ሸበሌ እና በጥቂት የላይኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ መጠን የሚደርስ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል፡፡ ይህም ሁኔታ በተለይም ቀደም ሲል ከተከማቸው የውሃ ሀብት ጋር ተዳምሮ በተፋሰሶች፣ በግድቦችና በውሃ ማከማቻዎች ያለውን የውሃ አቅም ለማጎልበት ጥሩ እድል ይፈጥራል። በተመሳሳይ ሁኔታ የደለል ስጋት ያለባቸውን እንደ ግልገል ጊቤ እና ቆቃ ግድቦች ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። በተጨማሪም አልፎ አልፎ ሊኖር ከሚችለው ተደጋጋሚ

ከባድ ዝናብ ሁኔታ ጋር ተያይዞ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ፣ እንዲሁም የወንዞች መሙላት በተለይም በኦሞ ጊቤ፣ በላይኛው ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽና በባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ላይ በከተማም ሆነ በወንዝ ዳርቻ፣ በረባዳማ እና ረግረጋማ አካባቢዎች የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች አስፈላጊ የቅድመ የጥንቃቄ ዝግጅት እንዲደረግ ይመከራል። በመሆኑም የዘርፉ አካላት የውሃ ሀብትን ለማጎልበት የሚኖረውን መልካም አጋጣሚ በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም እንዲሁም ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስ ብሎም ለማስቀረት የሚያስችል የጎርፍ መውረጃ ቦዮችን ማፅዳት፣ የጎርፍ መቀለበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት፣ ፍሳሽ መውረጃዎችን ሊዘጉ የሚችሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን በተገቢ ሁኔታ ማስወገድ፣ ወራጅ ውሃን ለማቋረጥ አለመሞከር፣ ለጎረፍ ተጋላጭ በሆኑ ቦታዎች ላይ የቅርብ ክትትል ማድረግ፣ በሌላ በኩል ዉሃ አጠር በሆኑ አካባቢዎች የዝናብ ውሃ ማሰባሰብና በተገቢዉ ሁኔታ በማጠራቀም በደረቅ ሰሞናት ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።

2.3 ከኦገስት 1/2025 እስከ ሴፕቴምብር 30/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪዎቹ ሁለት የክረምት ወራት በተለይም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብ፣ የደቡብ ምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የሰሜን፣ የመካከለኛው እና የሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ለወባ ትንኝ መራባትና ስርጭት ምቹ የአየር ሁኔታ እንደሚኖር ይጠበቃል። ከዚህም ጋር ተያይዞ የመካከለኛወና የምዕራብ ጎንደር፣ አዊ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ ኢሉ አባ ቦራ፣ ሁሉም የጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ ሁሉም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ ኮንታ፣ ጎፋ እና ዳውሮ ዞኖች ውስጥ የሚገኙ የወባ ተጋላጭ የሆኑ ቆላማ አካባቢዎች በከፍተኛ ደረጃ የወባ በሽታ ስጋት (High Malaria Risk) እንደሚኖር ይጠበቃል። በተመሳሳይ ሁኔታ የትግራይ ክልል ዞኖች፣ ሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ ሁሉም የጎጃም ዞኖችና ባህር ዳር ዙሪያ፣ የሰሜንና የደቡብ ወሎ ምሥራቃዊ ድንበር አካባቢዎች፣ ዋግህምራ፣ ምሥራቅና ምዕራብ ሸዋ፣ ጅማ፣ አርሲ፣ ምሥራቅና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ሀድያ፣ ጉራጌ፣ ድሬዳዋ፣ የሶማሌ ክልል ሲቲ ዞን እንዲሁም ከአፋር ክልል ጋቢ፣ ሀሪ እና ማሂ ዞኖች ውስጥ የሚገኙ የወባ ተጋላጭ የሆኑ ቆላማ አካባቢዎች በመካከለኛ ደረጃ የወባ በሽታ ስጋት (Moderate Risk) እንደሚጨምር ይጠበቃል። በእነዚህ አካባቢዎች የአየር ሁኔታው ለወባና ለሌሎች በትንኝ ለሚተላለፉ በሽታዎች ስርጭት ምቹ

Ethiopian Meteorology Institute

ስለሚሆን፣ የቅድመ መከላከል ሥራዎች ላየ ትኩረት በማደረግ፣ የቬክተር ቁጥጥርን ማሳደግ እና የጤና ክትትልን ማጠናከር ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል የዴንጊ ትኩሳት በሽታ በድሬዳዋ፣ በአፋር፣ በሶማሌ ክልል እና በምሥራቅ ኦሮሚያ አካባቢዎች ከፍተኛ የመከሰት እድል ሊኖር ስለሚችል የሚመለከታቸው አካላት በመቀናጀትና ህብረሰተሰቡን በማሳተፍ የትንኝ መራቢያ ስፍራዎችን ማጽዳት፣ የማህበረሰብ ግንዛቤን ማሰጨበጥ፣ የቅድመ ማንቂያና የጤና ክትትል ሥርዓቶችን ማጠናከር ያስፈልጋል። በአጠቃላይ በመጪዎቹ ሁለት የክረምት ወራት በወባ፣ በዴንጊ፣ በኮሌራ እና በሙቀት ጭንቀት ዙሪያ የሚጠበቁ ስጋቶችን ለመቀነስ በጤና ዘርፉ ላይ ሚና ያላቸው አካላትና ማህበረሰቡ በተቀናጀ ሁኔታ የቅድመ መከላከል ሥራዎችን ማጠናከር ይገባቸዋል።

ለበለጠ መረጃ የኢንስቲትዩቱን ድህረገጽ www.ethiomet.gov.et ይጎብኙ